KINIJIT INTERNATIONAL ADVISORY BOARD ■ ቅንጅት ዓለም አቀፍ አማካሪ ቦረድ
1629 K Street, NW, Suite 300, Washington, DC 20006
Tel (202) 973-0170, Fax (202) 3313759

## ከቅንጅት ዓለም አቀፍ አማካሪ ቦርድ የወጣ መግለጫ

ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም

# የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መስጠት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መድፈር ነው

ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርጋት ነገር ሕዝቦቿ የአገራቸውን ሉዐላዊነትና ዳር ድንበር ለማስከበር የከፈሉት ታላቅ መስዋዕትነት ነው:: ምንም እንኳን ላለፉት 17 ዓመታት በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ/ኢሕአዴግ ቡድን ይህን አኩሪ ገድልና የኢትዮጵያንም ከ3 ሺ ዘመናት በላይ ያስቆጠረ የሥልጣኔ ታሪክ ሲክድና ሲያስክድ ቢቆይም፤ ኢትዮጵያ ጥንት የነበረች፣ አሁንም ያለች፣ ወደፊትም በልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም የምትኖር ታላቅ፣ ጥንታዊና ታሪካዊ አገር ናት::

በዚህም የልጆቿ ከፍተኛ መስዋዕትነት ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከማስነበሯም በላይ በአቅኚዎች ግፍና በደል በአፍሪካ፣ በሰሜን አሜሪካና በካረቢያን ይሰቃዩ ለነበሩ ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ጎኅ፣ ተስፋና ተምሳሌት ሆና ቆይታለች:: ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከመያዙ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት ሁሉ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበርና ለማስጠበቅ በጣም የጠበቀና የማያወላውል አቋም ነበራቸው:: አቋማቸውንም በሥራ ተርጉመው አሳይተዋል:: ዛሬም የኢትዮጵያ ልጆች ሉዐላዊነቷንና ዳር ድንበሯን ለማስጠበቅ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው:: ይህንንም ለማወቅ ዛሬ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የኢትዮጵያ ልጆች ወያኔ/ኢሕአዴግና የሱዳን መንግሥት የኢትዮጵያን ሰፊና ለም መሬት ለሱዳን ለመስጠ ት በምስጢርና በድብቅ የተደረገውን የአገር ቆርጦ መስጠትን በመቃወም የሚደረገውን ንቅናቄ መመልከት በቂ ነው::

ስለሆነም የቅንጅት ዓለም አቀፍ አማካሪ ቦርድ ይህንን በስውርና በምስጢር ከሰሜን ጎንደር እስከ ጋምቤላ ያለውን 1600 ኪሎ ሜትር የሆነ የኢትዮጵያን መሬት ወያኔ ቆርጦ ለሱዳን መስጠቱን እጅግ በጠነከረ መልክ ይቃወማል፣ ይኮንናል:: ይህ ወያኔ/ኢሕአዴግ በስውርና በምስጢር ቆርጦ ለሱዳን የሰጠው መሬት የሕግም ሆነ የታሪክ ተቀባይነት የለውም:: ይህ የአገር ክህደት ወንጀል እስካሁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ

አልተገለጠለትም። ወያኔ/ኢሕአዴግ እንደ አሻንጉሊት የሚጠቀምበትም ፓርላማ ተብዬው እንኳ መሬት ተቆርጦ ለሱዳን መስጠቱን አያውቅም። በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ ይህ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ጉዳይ ነው። ይህም ሆኖ ጉዳዩ የአደባባይ ምስጢር ከሆነና ከእርስታቸው የተፈናቀሉትና በሱዳን በእስር የነበሩት ኢትዮጵያውያን በተለያየ ጊዜ ከአረጋገጡም በኋላ ወያኔ/ኢሕአዴግ አሁንም መሬት ቆርጬ ለሱዳን አልሰጠሁም እያለ በአደባባይ ይምላል ይገዘታል። ዞር ብሎ ደግሞ የተሰጠው መሬት የቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥታት በፈረሙት ውል መሠረት ነው ይላል። ውሸትና ክህደት የወያኔ/ኢሕአዴግ የተለመዱ ባህርያት ናቸው። በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በተካሄደው ጦርነት ጊዜና ከዚያም በኋላ ታየቷል። በግንቦት 15 ቀን 2005 በተደረገው ጠቅላላና የክልል ምርጫ ተያይዞ የተደረገው ግድያ፣ እስር፣ እንግልትና አጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ፣ ውሸትና ክህደት ሌላው የቅርብ ግዜ ምሳሌ ነው።

የሕግ የበላይነት የሌለበትና ቅጥ ያጣ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በሚካሄድበት አገር በሥልጣን ያለው ቡድን እሱ የሚፈልገውን ከማድረግ የሚያቆመው ምንም ነገር የለም። ስለዚህም ነው ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት በየጊዜው የሚሸረሽረው። ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የቆመ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ክህደትና ወንጀል ባልተፈጸመም ነበር።

የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ወያኔ/ኢሕአዴግ የፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነተና የግዛት አንድነት በመጣስ ላይ ናቸው። ብለውም ከሆነላቸው መሬታችንን ወንዞቻችንን፣ ጅረቶቻችንን ለመቆጣጠር ትልቅ ምኞትና ዓላማ እንዳላቸው ግልጽ ነው። ሥልጣኑን የያዘው ወያኔ/ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን እንደሚያፈራርስና እንደሚያጠፋ ግልጽ ነው።

ምንም እንኳን በድርጅቱና በአመራሩ ላይ ከፍ ያለ ጥቃት ቢካሄድበትም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ ምን ጊዜም ቢሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ይቆማል። ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነት፣ ለግዛቷ አንድነትና ለነጻነቷ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ማንኛውንም መስዋዕትነት ይከፍላል። ስለሆነም ከዚህ የሚከተሉት መሠረታዊ እምነቶቹን ይገልጻል፤

- የፖለቲካ፣ የሀይማኖት፣ የሲቪክ፣ የሙያ፣ የትምህርት፣ የመገናኛ ብዙሀን ክፍሎችና እያንዳንዱም ኢትዮጵያዊ ይህን የኢትዮጵያን መሬት ቆርጦ ለሱዳን መስጠትና የኢትዮጵያን መፈራረስ አጥብቆ እንዲቃወምና ተግቶም አገሩን እንዲጠብቅ፤

- ኢትዮጵያኖች ሁሉ የአገራቸውን ታሪካዊ ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት መጠበቅና ማስከበር፣ ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤

- በዚሁ ለሱዳን በተሰጠው መሬት ከርስታቸውና ከቀበሌያቸው እንዲፈናቀሉ ተደርጎ ግፍና መከራ ለሚፈጸምባቸው ወገኖቻችን ሁላችንም በያለንበት ተቃውሞ ለማድረግ የዜግነትና የሞራል ግዴታ ያስገድደናል።

- ወያኔ/ኢሕአዴግ በዘር፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት እየከፋፈለ ኢትዮጵያኖችን እርስ በእርስ እንድንተላለቅ የሚያደርገውን ተንኮልና ሤራ ተባብረን እጅ ለእጅ በመያያዝ መቃወምና ማክሸፍ ይኖርብናል:: ወያኔ በሥልጣን ሊቆይ የሚችለው እኛን ሲከፋፍልና እርስ በእርስ ሲያባላን ነውና ለዚህ ሰይጣናዊ መሳሪያ አንሁን።

- የተቃዋሚ ቡድኖችና የሲቪክ ተቋማት የኢትዮጵያን ነጻነት፣ ጥቅም፣ የግዛት አንድነት፣ ሉዐላዊነት፣ የሰብዓዊ መብቶችን፣ ስለሕዝብ ድምጽና ተሳትፎ ገንቢ ውይይት እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል።

- የሱዳን መንግሥት የኢትዮጵያንና የሱዳን ሕዝቦችን የእሩቅ ጊዜ ጥቅም በማጤን የኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት እንዲያከብር ጥሪ እናቀርባለን።

- እስካሁን ይህንን በሥውርና በምስጢር የተከናወነውን የአገርና የሕዝብ ክህደት በመከታተል ለኢትዮጵያኖችና ለውጭው ዓለም ያጋለጡትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ከልብ እናመሰግናለን:: በጋራም ይህ ቡድን የሚፈጽመውን የአገር ክህደትና የሰብዓዊ መብት ረገጣ መቋቋም ያስፈልጋል::

Reference: http://www.voanews.com/english/2008-06-05-voa43.cfm

# Ethiopia Map 1952-1993

http://www.lib.utexas.edu/maps/africa/ethiopia.gif

